እስመ በትሕትና

“ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች” ምሳሌ 11÷2



በዛሬው መጽሔታችን :-

1,ትሕትና ለቅምሻ
2, ትሕትና እና ድንግል ማርያም
3, ትሕትና እና ነገረ ድኅነት

For I tell you. Unless your righteousness exceeds that of the scribes and “Pharisees, you will never enter the kingdom of heaven. (Matthew 5÷20) Pharisees thought they kept the law by being zealous in teaching it. They did not realize they were breaking it by their wicked life. Education without work is considered breaking the law, and the teaching will be of no avail. Also working without witnessing before others decreases the reward.“Let your light so shine before men, that they may see your good works and glorify your Father in heaven.” (Matthew 5:16)

ቀናተኛ ሁነው በማስተማራቸው ፈሪሳውያን ሕጉን የጠበቁ ይመስላቸዋል፤ ነገር ግን ይሀንን አይስተውሉም በክፉ ወይም በተበላሸ አኗኗራቸው የሚያስተምሩትን ሕግ እንደሚያፈርሱ። አስተምህሮ ያለ ሥራ ሕግን እንደመሻር ይቆጠራል እናም ማስተማሩ ምንም አይጠቅምም። እንዲሁም ሥራ ያለመመስከር (ያለ አርአያነት) ከሆነ ሌሎች ክብሩን አሳንሰው ያዩታል። "መልካሙን ሥራችኹን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችኹን እንዲያከብሩ ብርሃናችኹ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" (ማቴ 5÷16) እንዲል መጽሐፍ።

ትሕትና ለቅምሻ..

በገነተ አበው *(The paradise of Father's)* አንድ መነኩሴ በበአቱ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነብ አንድ ቃል ሊገባው አልቻለም፤ ለመረዳት ሲያስቸግረው "ይኼን ቃልስ እንዲገልጽልኝ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለብኝ" ብሎ ወሰነ። ነቢያቱ ያደርጉት እንደነበረውም እግዚአብሔር የቃሉን ፍቺ እስኪገልጽለት ድረስ መጾምና መጸለይ ጀመረ። ነገር ግን ለሰባ ሳምንታት ያህል እየጽመ ቢጠባበቅም ምንም ነገር ሊገለጽለት አልቻለም። በየሳምንቱ መጨረሻ ቃሉን ደግሞ ሲያነበውም የበለጠ እየተወሳሰበበት ሔደ እንጂ ጨርሶ ሊገባው አልቻለም፤ በመጨረሻም ተስፋ ቆረጠ። ስለዚህ ሌላ መነኩሴ ጋር ሔዶ ስለዚህ ቃል ትርጉም ሊጠይቀው ወሰነ። በአቱን ዘግቶ መንገድ ሊጀምር ሲዞር ግን የእግዚአብሔር መልአክ በፊቱ ቆሞ ታየው፤ " አይዞህ አትፍራ የፈለግኸውን የቃሉን ትርጉም ልገልጽልህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኬያለሁ" አለው። መነኩሴውም ግራ በመጋባት "የጌታ መልአክ ሆይ ሰባ ሳምንት ሙሉ እየጾምሁ እንዲገለጥልኝ ስለምን ቆይቼ ምንም መልስ አላገኘሁም፤ ታዲያ አሁን ተስፋ ስቆርጥ እግዚአብሔር ስለምን መለሰልኝ *?*" አለ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ ፡ መልአኩም "እግዚአብሔር ሰባ ሳምንታት ከጾምኸው ጾም ይልቅ ወንድምህን ለመጠየቅ ለመሔድ ያሳየኸውን ትሕትና ተቀብሎታል" አለው። ትዕቢት ማለት አይን እያለህ የጌታን ተአምር እያየህ እንደ አይሁዳውያን እውር እንደመሆን ፣ ጆሮ እያለህ የጌታን ቃል እንዳፈሰሰው ይሁዳ ፣ ልብ እያለህ የእግዚአብሔር መቅሰፍት እንዳልመለሰው ልቡ እንደደነደነበት ፈርዖን መሆን ነው። "ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች"*(ምሳሌ 11፥2)* እንደተባለ በመጽሐፍ። ቅዱስ አውግስጢኖስ በአንድ ወቅት "ለድኅነት መሠረታዊ የምትላቸው ነገሮች ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ *:- 1*ኛ ትሕትና ፣ *2*ኛ ትሕትና ፣ *3*ተኛ ትሕትና ብሎ መልሷል። ትሕትና የሌለው ሰው ድኅነትን አያገኝም / ለዛ አብዛኞቻችን ንስሐ የማንገባው የትሕትና ፍሬ በልባችን ስላልበቀለ ነው፤ "ትሑት ማለት እኔ ኃጢአተኛ ነኝ" እያሉ እዛው በኃጢአት ውስጥ መመላለስ ማለት ሳይሆን የበደሉትን አምላክ በንስሐ ማስደሰት ነው ትሕትና የሚባለው። ትሑት የሆነ ሰው ጸጋ እግዚአብሔር ይጨመርለታል፤ "እግዚአብሔር ትዕቢተኞዎችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል፤" *(1*ኛ ጴጥ *5 - 5 - 6)* ያለ ትሕትና የሚደረግ መልካም ነገር ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር አይቀበለውም። የፈለገውን ያህል እውቀት ቢኖርህ ትሕትና ግን ከሌለህ እንደሚጮህ ገደል ማሚቱ ነህ የተጫነብህን እውቀት ነውና እያስተጋባህ ያለኸው ፣ የፈለገውን ያህል ጸሎተኛ ብትሆን በቀን *1000* ሺህ ስግደት ብትሰግድ ትሕትና ከሌለህ ላብ በላብ ከመሆን በስተቀር አንድም ምታገኘው ዋጋ የለም ፣ የፈለገውን ያህል ጾመኛ ልትሆን ትችላለህ ነገር ግን ጾምህ በፍቅር ና በትሕትና ካልተመላ እንደ ፈሪሳዊው በመቅደስ መጥተህ በሳምንት ይሄን ያህል እጾማለሁ እንደነዚህ ሰዎች ስላላረከኝ አመሰግናለሁ እያልክ ከመታበይ ውጪ ምንም አይጠቅምህም። ክርስቶስ ለአንተ በረት ውስጥ ሚወለድበት አጥቶ ተወለደ ተብሎ እየተነገረህ ምን ያኮራሀል እርሱ ሁሉን ማድረግ እየቻለ እራሱን ባዶ ካደረገ አንተ ምንም ያለእርሱ ማድረግ የማትችለው ፍጥረትማ ምን ያህል ራስህን ስለከፈለልህ ውለታ ልታዋርደው ይገባ ይሆን *?*

ትሕትና እና ድንግል ማርያም

እመቤታችን ፍጽምት ንጽሕት እንዲሁም እጅግ ትሑት ነች፤ ከፍጥረት ሁሉ ተለይታ ፈጣሪዋን ለመውለድ ወላዲተ አምላክ ለመሆን የተመረጠችበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት የአምላክ እናት እንደምትሆን ተነግሯት እንኳን እመቤታችን "የባሪያይቱን መዋረድ ተመልክቷልና" በማለት በትሕትና ነበር ምስጋናዋን ያቀረበችው፤(ሉቃ.፩÷፵፰) ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ "እርሷ በእግዚአብሔር ዓይን በታየ የቅድስና ውበት የተሞላች ነበረችና በእርሷ ንጹሕ ማሕፀን ሊያድር ወደደ፤ እንደ ድንግል ማርያም ራሱን ዝቅ ያደረገ ትሑት ማንም የለም" ይላል። ቅዱስ ኤፍሬም "በትሕትና የተናገርሽ ተራራ ሆይ..." ብሎ ያመሰገናት ይህች ድንግል እንደ ተራራ ከፍ ያለች ስትሆን ራሷን እንደ ሸለቆ ዝቅ አድርጋ "እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን ይደረግልኛል" ብላ በልብዋ አሰበች፤ በዚህ በእናታችን ትሕትና እጅግ እንደነቃለን፤ ‹‹ድንግል ሆይ እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንምን አይደረግልሽም?›› የተመረጥሽው የሰማይና ምድርን ፈጣሪ ልትወልጂ አይደለም ወይ? እሳተ መለኮትን ተሸክነመሸ፣ ሰማይና ምድር የማይችሉትን ችለሽ እንዲህ ያለ የምስጋና እጅ መንሻ እንደምን አይደረግልሽም? እያልንም እናመሰግናታለን። እመቤታችን ቅድስት ማርያም ጸጋን የተሞላች በእግዚአብሔር ፊት ባለሟል የሆነች፥ ልጇ አምላኳ አምላኳ ልጇ የሆነላት ባለሞገስ ነችና በምልጃዋ አምነው በንስሓ ሆነው ለሚማጸኗት ከእርሷ የተሻለ አማላጅ ከወዴት ይገኛል።

Why God Choose Mary

"The humility of Mary became the ladder by which God descended to earth."

St.Augustine

"የእመቤታችን ትሕትና እግዚአብሔር ወደ ምድር እንዲወርድ መሰላል ሆነው፤"



"በእባቡ ፈንታ ገብርኤል ሊናገር ተነሳ፤ በሔዋንም ምትክ ማርያም ተነሳች በሃሳቡ ልትስማማ ሁለት መልእክተኞች ወደ ሁለት ድንግሎች ተላኩ፣ሰይጣን ምስጢርን ለሄዋን በእባቡ በኩል ነገረ፤ ጌታም በመልአኩ በኩል የምስራቹን ለእመቤታችን ላከ"

ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ

ዛሬስ የማንን ምክር ተቀብለን ይሆን ? ህይወታችን አሁን ላለበት ውጥንቅጥ ማን ይሆን ተጠያቂው ? እንዴትስ ነው አሁን ላይ የመልአክ ብስራት ልሰማ የምችለው እያልክ እየተብሰለሰልክ ይሆን ? መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ያበሰራት ወንጌል ነበር፤ አንተም ወንጌልን በሕይወትህ ከገለጥኸው ፈለገ ማርያምን ተከተልክ ማለት ነው። ወንጌል ይነበባል ፣ ወንጌል ይረዱታል ፣ ወንጌል ይኖሩታል። በየትኛው ደረጃ ላይ ነህ ? ወንጌልን ታነባለህ ፣ ወንጌልን ከማንበብ ከፍ ብለህ ትረዳዋለህ ወይስ ከመረዳትም አልፈህ እየኖርከው ነው ? ሶስቱንም ደረጃዎች ለመውጣት ከድንግል ማርያም የትሕትናን ልብ ልጠይቅ ይገባል። ምክንያቱም ከጌታ በቀር ዓለም ላይ ከእሷ በላይ ትሑት የሆነ የለምና።

ምክረ ድንግል ማርያም

1, ከአንተ ይልቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚሻል እወቅ፤ ዛሬ ላይ እያስለቀሰህ ያለ የትኛውም ነገር ከገሃነመ እሳት ልቅሶ እንድተርፍ የማንቂያ ደውል ነውና እግዚአብሔርን እያማረርክ የእንፋሎት እድሜህን አትጨርሰው

2, ልበ ደንዳና አትሁን ነገር ግን ያገኘኸውን ፣ የሰማኸውን ፣ ያየኸውን ነገር ሁሉ ሳትመዝን ፣ ሳታጣራ አሜን ብለህ አትቀበል። ሁለት አይነት አሜናት አሉ አንዱ ለምርቃት አንዱ ለጥፋት

3, ከአፍህ በላይ ህይወትህ ይናገር ! ማንንም ለማሳመን አትውጣ ፣ አትውረድ ዋናው ጉዳይ እግዚአብሔር ከተረዳህ በቂ ነው፤ በሚታየው ነገር ብቻ ከሚፈርድብህ ሰው ይልቅ ውስጥህንም የሚያውቀውን ክርስቶስን ብቻ ፍራ።

ትሕትና እና ነገረ ድኅነት

ትሕትና የነገረ ድኅነት በር ነው። ያለ ትሕትና ነገረ ድኅነት ማሰብ ጌታ ለእኛ ያደረገውን እንደመካድ ነው፤ ትዕቢት ደግሞ የውድቀት ሁሉ ሥር ነው። ትዕቢት ማለት የጸጋ ሌባ ረቂቅ ጠላት ነው። ነገር ግን ትሕትና ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድ እንዲሁም ፍቅራችንን የምናሳይበት ፣ ሰይጣንን ድል የምንነሳበት ኃያል ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ተፈጣሪ ምስለ አምላክ (አምላክን የመምሰል) ስጦታ ነው። ትሕትና ማለት እኛ በአምላክ ፊት ድካማችንን መግለጫ አምላካችን ደግሞ ለእኛ የሚያሳየን ምሕረት መተሳሰሪያ ፈለግ ነው። ትዕቢተኛ ሰው ድኅነትን አያገኝም። ምክንያቱም ትሕትና ማለት መስቀል መሸከም ስለሆነ ፣ ትሕትና ማለት ራቆትህን እንደጌታ በሚሰድቡህ ፊት መቆም ስለሆነ ፣ ትሕትና ማለት የሚወጉህን ይቅር ማለት ስለሆነ ፣ ትሕትና ማለት ስለ ሰው ሁሉ እየተጨነቁ መራራን ሐሞት መጠጣት ስለሆነ ፣ ትሕትና ማለት ሁሉ እያለህ ፣ መናገር እየቻልክ ያለ በደልህ ስትከሰስ ዋጋ መንግስተ ሰማያትን እያሰቡ ዕለተ ዓርብን ከክርስቶስ ጋር ማሳለፍ ስለሆነ።

"እግዚአብሔር ትዕቢተኛዎችን ይቃወማል፤ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል።"

የያዕቆብ መልእክት 4÷6